ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል

Moa Anbessa

10/03/98

ሞዓ አንበሳ የዘውድ ደጋፊዎች ፓርቲ (ሞዓዘደፓ)
የሥራ ፕሮግራም (ባጭሩ የወጣ)

የዘውድ ንቅናቄ በሀገርም ውስጥ ሆነ በውጭ በበለጠ እንዲጠናከር አስፈላጊነቱን መነሻ በማድረግ ÷ የዘውድ ምክር ቤትና የሞዓ አንበሳ ድርጅት ግንኙነት በአዲስ ሁኔታ እንዲመሠረትም ወቅቱ የሚጠይቅ መሆኑን በመገንዘብ÷ ሞዓ አንበሳ እራሱን የቻለ ፓርቲ ሆኖ እንዲሠራ የሚያስችለው ፕሮግራም እንዲሚከተለው ቀርቡዋል::

ይህ ፕሮግራም መጀመሪያ ሰኔ 29 ቀን /91 ዓ.ም ግርማዊ ቀዳማዊ አመሐ ሥላሴ በተገኙበት በካፒቶል ሂልተን ዋሽንግተን ዲሲ በተደረገው የሞዓ አነበሳ ምሥረታ ታላቅ ስብሰባ እና ከዚያም በግርማዊነታቸው መልዕክተኞች ጥሪ አዲስ አበባ ላይ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትያትር አዳራሽ ውስጥ ኅዳር 15 ቀን /91 ዓ.ም በተደረገው ታላቅ የሕዝብ ስብሰባ በዝርዝር ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተገለጠውን የስራ ፕሮግራም ያጠቃልላል::

አሁን ሞዓ አንበሳ ከዙፋናዊ አሰባሳቢ አካልነት ወደ ዘውድ ደጋፊዎች ፓርቲነት (ዘደፓ) ሲሸጋገር በቤተ መንግሥቱ ከድህረ ዓምሐ ሥላሴ በኋላ የተከሰቱትን ሁኔታዎችና በአገሪቱም ላይ የመጣውን ለውጥ ሁሉ ከግንዛቤ በማግባት የፓለቲካ÷ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ፕሮግራሙን ለወቅቱ ተስማሚ በሆነ መንገድ እነሆ ቀይሷል:: ከፖለቲካ÷ ከኢኮኖሚና ከማህበራዊ ኑሮ ፕሮግራሞቹ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

የዘደፓ የፖለቲካ ፕሮግራም

ሕገ መንግሥታዊ የዘውድ አስተዳድር ወይም በእንግሊዘኛው አጠራር "ኮንስቲቱሽናል ሞናርኪ' በሕግ በተወሰነ የደንብ ክልል ውስጥ የስልጣን ገደብ ተደርጎለት የሚሰራ ሕገመንግሥታዊ አስተዳደር በኢትዮጵያ እንዲቋቋም በመካሄድ ላይ ያለውን ትግል ዘደፓ ግንባር ቀደም በመሆን ስራውን ያከናውናል:: ይህንንም እውን ለማድረግ የሚከተሉትን አንቀጾች ያጠቃልላል::

ሀ. ዘውድ የኢትዮጵያ ታሪካዊ መታወቂያ በመሆኑ የሺ ዘመናት ስረወ መንግሥቱን ተከትሎ ከትውልድ ወደ ትውልድ በመተላለፍ የሕዝቧን ልዕልናና የአገሪቱን ሉዑላዊነት የሚረጋገጥበትና የዘውድ አገር መሆኗም በግልጽ ይቀረጻል::

ለ. ዘውድ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አሰባሳቢ አካል በመሆን የአገሪቱን አንድነትና ሰላም በማስጠበቅ ከፍተኛና ወደር የሌለው አስተዋጽዖ ሲያበረክት የኖረ ኃይል መሆኑና አስፈላጊነቱ ይረጋገጣል ::

ሐ. ዘውድ ከታሪካዊ ቅርስነቱ ባሻገር ለሰላምና ለኢኮኖሚ ግንባታ ለውጭ ኢንቨስተሮችና ኢንተርፕረነሮች አሰተማማኝ ዋስትና መሆኑም ያረጋግጣል ::

መ. ዘውድ [illegible] ንድነትና በሕግ ልዕልና ላይ የተመሠረተ ይሆናል ::

ሠ. በአጠቃላይም [illegible]ሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ እ.ኤ.አ. በዲሴምበር 10 ቀን 1948 ዓ.ም የአደቀውንና የታወጀውን ቁጥር 217 ውሳኔ መሠረት በማድረግ የግለሰብ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለአንዳች ገደብ ሙሉ በሙሉ የሚከበሩበት መሆኑን ያረጋገጣል::

ረ. የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፥ ነፃነትና ፀጥታ የሚያስጠብቅ ከፓለቲካ ተፅዕኖ ነፃ የሆነ የመከላከያ ጦርና የፖሊስ ሠራዊት ይቋቋማል:: እንደዚሁም ከማናቸውም የፓለቲካ ተፅእኖ ነፃ የሆኑ ፍርድ ቤቶችና የሕግ ተቋሞች ይመሠረታሉ::

ሰ. የዘደፓ ዋና ተግባር በአገር ውስጥ የሚያተኩር ስለሆነ ሥራውን በበለጠ ለማበረታታት አዲስ አበባ ያለውን ቢሮ በአዲስ የሰውና የገንዘብ ኃይል ያጠናክራል፤ አሁን ባሉት ላይ ተጨማሪ ቅርንጫፎችንም እንደአስፈላጊነቱ ይከፍታል::

ሸ. ዘደፓ የኢትዮጵያን ቋንቋንዎችና ክፍል ግዛት ባሕሎች ሁሉ ከፍተኛ እንክብካቤ ሊደረግላቸው የሚገባ እንደ ትልቅ ሀብት አድርጎ ይመለከታቸዋል:: ስለዚህም በእኩልነት በንግግርና በሥነጽሁፍ ጥበብ እንዲስፋፉ ያደርጋል:: ይህም ከታሪክ የተወረሠውንና አብዛኛው ሕዝብ የሚጠቀምበትን የግዕዝ ፊደልና ስነ ጽሁፍ፥ እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ የሆነውን አማርኛ የበለጠ የሚያበለፅግ መሆኑን ያምንበታል::

ቀ. በማንኛውም የባዕድ ኀይል ተጽዕኖ ስር የማይወድቅ፥ በሰላም አብሮ በመኖርና ለአህጉራዊም ሆነ አለምአቀፋዊ ድርጅቶች ድንጋጌዎችና ስምምነቶች አስተዋጽኦ የሚያደርግ፥ በገለልተኝነት ላይ የተመሠረተ የውጭ ግንኙነት ፓሊሲ ይከተላል::

በ. እነዚህንም መሠረታዊ ሀሳቦችን የሚያጠናክሩ፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ሰላም አዎንታዊ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ህጎችና ደንቦችን ሁሉ በሚያጠቃልል ሕገመንግሥት የሚመራ ይሆናል::

<u>የዘደፓ የኤኮኖሚ ፕሮግራም</u>

የዘደፓ የኤኮኖሚ ፕሮግራም መነሻ የሚሆነው ጥንታዊውና በነገሥታቱ ሲታወጅ በቆየው "የሞትንም እኛ ያለንም እኛ፥ ገበሬም እረስ፥ ነጋዴም ነግድ፥ ሁልህም ባለህበት እርጋ" ከሚለው አነጋገር የተወሰደ ሲሆን ኢኮኖሚው በክፍት ነጻ ገበያ ላይ የተመሠረተ ሆኖ የሚከተሉትን አርእስተ ነገሮች ያጠቃልላል::

ሀ. የአገሪቱ ምጣኔ ሀብት ከሕዝቡ ብዛትና የኑሮ ደረጃ ጋር የተመጣጠነ እድገት እንዲኖረው፥ ሕዝቡ በሙሉ ያለአንዳች መገታት የጉልበትና የአዕምሮ ፈጠራ ስራውን እያከናወነ አገሩን እንዲገነባ፥ ከቦታ ቦታ እንደልቡ እየተዘዋወረ የመስራት ነፃነቱንም የተረጋገጠ እንዲሆንለት ፓርቲው በብርቱ ይጥራል::

ለ. መሬት በአገራችን አንዱ ትልቁ የሀብት ምንጭ መሆኑ የታወቀ ከመሆኑም በላይ የአብዛኛው ሕዝብ በተለይም የገበሬው የኑሮው መሠረትና አለኝታ ስለሆነ እንዳገሩ ስሪትና ልማድ አስፈላጊው እንክብካቤ እየተደረገለት ጦሙን ሳያድር በልማት

እንዲጠበቅ ያስፈልጋል:: ለዚህም የባለቤትነት መብት የተጠበቀ ሆኖ የመውረስ የማውረስ፥ የመሸጥ የመለወጥ መብት ሙሉ በሙሉ እንዲከበር ያደርጋል::

ሐ. ያለአግባብ በመንግሥት የተወረሰ ቤት፥ ሀብትና ንብረት ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ ለባለቤቱ እንዲመለስ ያደርጋል::

መ. ከትንሽ እስከ ትልቅ የንግድና የፋብሪካ ቤቶችን የሚያቋቁሙ የአገር ውስጥና የውጭ ነጋዴዎች፥ ኢንቬስተሮችና ኢንተርፕረነሮች አስተማማኝ የሆነ ዋስትና ይሰጣል::

ሠ. ከመሬት ውስጥና ውጪ የሚገኙ ሀብቶች፥ ማዕድናት፥ ደኖች፥ ወንዛወንዞች፥ ሐይቆችና ባሕሮች ሁሉ የኢንተርናሽናል ሕግጋት እንደተከበሩ ሆኖ ለአገር ጥቅምና ለሕዝብ ብልጽግና እንዲውሉ ይደረጋል:: የአገሪቱ የተፈጥሮ ሀብትና ውበት፥ የዱር አራዊት፥ አእዋፍና አሦች በሰው ግፊት እንዳይጠፉ ዘደፓ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል::

ረ. የአገሪቱ የገንዘብ ይዞታ ከውጭ ምንዛሪ ውጣ ውረድ የተጠበቀ የሚያደርገው አስተማማኝ የኢኮኖሚ ዋስትና እንዲኖረውና፥ ከአለም ባንክና ከሌሎችም ድርጅቶችና አገሮች የሚገኘው የብድር ገንዘብ እስከ ልጅ ልጅ ድረስ የማይከፈል ዕዳ ውስጥ አገሪቱ እንዳትገባ ጥንቃቄ እንዲደረግ ይጥራል::

የዘደፓ የማሕበራዊ ኑሮ ፕሮግራም

የዘደፓ የማሕበራዊ ኑሮ ፕሮግራም የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዐላዊነት በማስቀደም በነፃነት በእኩልነት በፍትህና በመፈቃቀር ተከባብሮ አብሮ መኖርና ዲሞክራሲያዊ ሥርዐተ መንግሥት ተቋቁሞ ሕዝቡ በትምህርት እደገቱ በጤና አጠባበቁ በጠቅላላው በኑሮ ደረጃው የሚሻሻልበትን ዘዴና መንገድ ይተልማል:: ለዚህም የሰብአዊ መብቶች መከበርና የሃይማኖት ነፃነት መጠበቅ ዋና መሠረት ነው::

የኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የነፃነት ታሪክ የብሔረሰብዋ የጋራ ሀልውናና የጋራ ታሪኳ ስለሆነ ዘውድ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ እንደ አንድ ቤተሰብ አስተባብሮ የኖረ የሰላም፥ የፍቅር፥ የስምምነትና የአንድነት ምልክት በመሆኑ ሁሉን በማቀፍ አማራ፥ ኦሮሞ፥ ትግሬ፥ ጉራጌ ወላይታ...ወዘተ ሳይል እንደኖረ ዘደፓ ይህንኑ ፀባይ በማንፀባረቅ ሕዝቡ ታሪካዊ ቅርሱን አክብሮ በዘውድ ድባብ ስር ተሰባስቦ፥ በአንድነቱ ፀንቶ፥ ጦርነትን፥ መለያየትንና ዘረኛነትን አስወግዶ በሰላም እንዲኖር በርትቶ ይሰራል:: በዚህ ረገድ ከስራዎቹ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ይሆናሉ::

ሀ. ኢትዮጵያን ከአገሮች ሁሉ ልዩ የሚያደርጓት ታሪካዊ ልማዷ፥ ባህሏና ሃይማኖቷ፥ እንደዚሁም ፊደሏና የስነ ጽሁፍ፥ የቅኔና የዝማሬ ሀብቷ ከጥንታዊ ሐውልቶቿና ገዳማት ጋራ የመላው ዓለም ቅርስ ስለሆኑ አስፈላጊው ከበሬታ ተሰጥቷቸው ተጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ያደረጋል።

ለ. ሥራና ሠራተኞች ለአገር ልማትና ብልጽግና የጀርባ አጥንት ስለሆኑ፥ የአእምሮም ሆነ የእጅ ሥራ ሞያተኞችን ዘደፓ በልዩ እንክብካቤ ይይዛል:: የመደራጀትና በአገር ጉዳይ ሙሉ በሙሉ የመሳተፍ መብታቸውን ያስከብራል።

ሐ. "ሃይማኖት የግል አገር የጋራ ነው" የሚለውን ንጉሣዊ መርሆ ዘደፓ በሥራ ላይ ያውላል::